

## የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን

# የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ኢንተርኮኔክሽን መመሪያ

## ለባለድርሻ አካላት ምክክር የቀረበ ረቂቅ

ነሀሴ 2012

# የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ኢንተርኮኔክሽን መመሪያ

የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን በኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 ("አዋጁ") አንቀጽ 6(2) በኢትዮጵያ ውስጥ የኮሙኒኬሽን ፖሊሲዎችን የማስፈጸም ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ፤

በአዋጁ አንቀጽ 6(13) ባለሥልጣኑ በተለያዩ የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርኮች መካከል ያለውን ኢንተርኮኔክሽን የመቆጣጠር ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ፤

የአዋጁ አንቀጽ 43(1) በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች መካከል የሚደረጉ የቴሌኮሙኒኬሽን ስምምነቶች ሁሉ አዋጁን እና አዋጁን መሠረት አድርገው የሚወጡትን መመሪያዎች እንዲያከብሩ የሚያስገድድ በመሆኑ፤

በአዋጁ አንቀጽ 54(2) ባለሥልጣኑ አዋጁን እና አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም መመሪያዎች የማውጣት ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ፤

ባለሥልጣኑ ይህንን የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ኢንተርኮኔክሽን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## አጭር ርዕስ፣ ትርጓሜ፣ አላማ እና የተጻሚነት ወሰን

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ኢንተርኮኔክሽን መመሪያ ቁጥር 8/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ መመሪያ በጥቅም ላይ የዋሉ ቃላቶችና ሐረጎች በኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 የተሰጣቸው ትርጉም እና አፈጻጸም ይኖራቸዋል። የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1) **"ባለሥልጣን"** ማለት በኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን ነው፤
2) **"ኢንተርኮኔክሽን"** ማለት የአንድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ተጠቃሚዎች ከተመሳሳይ ወይም ከሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ተጠቃሚዎች ጋር እንዲገናኙ ወይም በሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የሚሰጡ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ የሚያስችል በተመሳሳይ ወይም ሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ጥቅም ላይ የዋሉ የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ አካላዊ፣ ቴክኒካዊ እና ምክንያታዊ ግንኙነት ማለት ነው፡ ፡ አገልግሎቶች በተሳተፉ አካላት ወይም የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ተደራሽነት ባላቸው አካላት ሊቀርቡ ይችላሉ።
3) **"አገናኝ ኦፕሬተሮች"** ማለት የየራሳቸውን የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትዎርኮች የሚያገናኙ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች ናቸው፤
4) **"ኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ"** ማለት ለሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የኢንተርኮኔክሽን አገልገሎቶችን የሚያቀርብ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ነው፤
5) **"የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎቶች"** ማለት የየራሳቸውን የኔትወርክ ግንኙነቶችን ለማሳካት አንድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ለሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር

የሚሰጣቸው አገልገሎቶች ናቸው፤ አባሪ አንድ የእነዚህን አገልግሎቶች ዝርዝር እና ማብራሪያዎች ይዟል፤

6) "የኢንተርኮኔክሽን ቦታ" ማለት ሁለት እና ከሁለት በላይ የሆኑ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተሮች ኔትወርኮች የሚገናኙበት በቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ውስጥ ያለ በጋራ ስምምነት የተደረሰበት ቦታ ነው፤

7) "የኢንተርኮኔክሽን አቅርቦት መነሻ ሰነድ" ማለት ለኢንተርኮኔክሽን ስምምነት የተዘጋጀ መደበኛ ቅፅ ነው፤

8) "ጠያቂ ኦፐሬተር" ማለት ከሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተር ኢንተርኮኔክሽን የሚጠየቅ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተር ነው፤

9) "ተጠያቂ ኦፐሬተር" ማለት ከሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተር የኢንተርኮኔክሽን ጥያቄ የሚቀበል የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተር ነው፤

10)"የቴሌኮሙኒኬሽን የችርቻሮ አገልግሎት" ማለት ለሌላ ቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተር ሳይሆን ለመጨረሻው ተጠቃሚ በቀጥታ የሚሰጥ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ነው፡ ፡

3. <u>ዓላማ</u>

1) የዚህ መመሪያ ዓላማ የኢንተርኮኔክሽን ስምምነቶች የሚገዙበትን ማዕቀፍ መደንገግ ነው፡፡

2) መመሪያው በተጨማሪ በአዋጁ አንቀጽ 42 እና አንቀጽ 43 መሠረት ባለሥልጣኑ የኢንተርኮኔክሽን ስምምነቶችን ለመቆጣጠር የሚከተላቸው ደንቦች እና ሥነ ሥርዓቶች ግልጽነት እነዲኖራቸው ማድረግ ነው፡፡

3) የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተሮች በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግዛት ውስጥ የተቀናጁ እና ወጥነት ያላቸው የቴሌኮሙኒከሽን አገልግሎቶች እንዲሰጡ ማስቻል ነው፡፡

4) እያንዳንዱ የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ተጠቃሚ ከሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ተጠቃሚ ጋር ግንኙነት እንዲያደርግ ማስቻል ነው፡፡

4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግዛት ውስጥ በሚገኙ በሁሉም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተሮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የባለሥልጣኑ ሚና

5. <u>የባለሥልጣኑ ሚና</u>

1) ባለሥልጣኑ

(ሀ) የኢንተርኮኔክሽን አለመግባባቶችን ለመፍታት ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ የተሟላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተሮች ኔትወርኮች ግንኙነት እንዲኖር ጥረት ያደርጋል፤

(ለ) በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተሮች መካከል የሚኖረውን ኢንተርኮኔክሽንን የሚገዙት ደንቦች በከፍተኛ ደረጃ ተአማኒነት እንዲኖራቸው ያደርጋል፤ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ገበያዎች ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳላቸው በባለሥልጣኑ

የተወሰነላቸው የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች የኢንተርኮኔክሽን አቅርቦት መነሻ ሰነድ በማዘጋጀት በባለሥልጣኑ እንዲያጸድቁ ትዕዛዝ ይሰጣል፤ እና

(ሐ) የኢንተርኮኔክሽን አቅርቦት መነሻ ሰነድ ከአዋጁ፣ ከዚህ መመሪያ እና በባለሥልጣኑ ጸድቀው ተፈጻሚነት ካላቸው ማናቸውም መመሪያ ድንጋጌዎች ጋር የተጣጠመ መሆኑን ገምግሞ ያጸድቃል።

2) በአዋጁ አንቀጽ 43 መሠረት ባለሥልጣኑ፤

(ሀ) የኢንተርኮኔክሽን ስምምነቶች ከአዋጁ፣ ከዚህ መመሪያ እና በባለሥልጣኑ ጸድቀው ተፈጻሚነት ካላቸው ማናቸውም መመሪያ ድንጋጌዎች ጋር የተጣጠመ መሆኑን ለማረጋገጥ ይገመግማል።

(ለ) በራሱ ጊዜ ወይም በኢንተርኮኔክሽን ስምምነት ተዋዋይ ወገን ሲጠየቅ ጣልቃ በመግባት በአዋጁ፤ በዚህ መመሪያ ወይም በባለስልጣኑ ተቀባይነት አግኝቶ ተግባራዊ የሆነ ማንኛውንም መመሪያ ጋር የማይጣጣሙ በኢንተርኮኔሽን ስምነቶች ያሉ ድንጋጌዎችን በመለወጥ አስገዳጅ ውሳኔዎችን ይሰጣል።

(ሐ) ተዋዋይ ወገኖች በኢንተርኮኔክሽን ድንጋጌዎችና ሁኔታዎች ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉ ወይም ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ወይም በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሠረት ኔትወርክ ማገናኘት ካልቻሉ በራሱ ተነሳሽነት ወይም በኢንተርኮኔክሽን ስምምነት ተዋዋይ ወገን ጠያቂነት ጣልቃ ሊገባ ይችላል፤ ተገቢ ሆኖ ከተገኘም የኢንተርኮኔክሽን ድንጋጌዎችና ሁኔታዎችን ይወስናል፤ ወይም

(መ) በራሱ ተነሳሽነት ወይም በኢንተርኮኔክሽን ስምምነት ተዋዋይ ወገን ጠያቂነት በዚህ መመሪያ በተደነገገው ያለመግባባቶች መፍቻ ሥርዓቶች መሠረት የኢንተርኮኔክሽን አለመግባባቶችን ለመፍታት ጣልቃ ሊገባ ይችላል።

## ክፍል ሦስት
## አጠቃላይ የኢንተርኮኔክሽን መርሆዎች

6. <u>ግልጽነት</u>

1) ባለሥልጣኑ በኢንተርኮኔክሽን ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ለመስጠት የሚያልፍባቸው ሂደቶች የሚታዩ እና ግልፅ መሆን አለባቸው።

2) በኢንተርኮኔክሽን አገልግሎቶች በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ገበያዎች ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው በባለሥልጣኑ የተወሰነለት የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር በባለሥልጣኑ የፀደቀውን የኢንተርኮኔክሽን አቅርቦት መነሻ ሰነድ እንዲታተም ማድረግ ይኖርበታል።

3) ባለሥልጣኑ ያፀደቀውን የኢንተርኮኔክሽን አቅርቦት መነሻ ሰነድ በድረ ገፁ ላይ ያወጣል፤ ተጠያቂው ኦፕሬተር ይህንኑ ለጠያቂው ኦፕሬተር ያለ ክፍያ ማቅረብ ይኖርበታል ።

7. <u>አድልዎ አለማድረግ</u>

አድልዎ ያለማድረግ መርህ የአገልግሎት የቴክኒክ ደረጃዎችን፣ አስተማማኝነትን፣ ጥራትን እና ክፍያን ጨምሮ የኢንተርኮኔክሽን ድንጋጌዎችና ሁኔታዎች እነዚህን የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎቶች ለራሱ ወይም ለሌላ ኦፕሬተር ከሚያቀርብበት አገልግሎቶች ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን ያስገድዳል።

8. <u>ሕጋዊ ክፍያዎች</u>

የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎቶች አቅራቢዎች የሚያስከፍሉት ክፍያዎች ትክክለኛ፣ ምክንያታዊ እና በተጠቃሚዎች ወይም በተጠቃሚዎች መደብ መካከል አድልዎ የማያደርጉ ሕጋዊ ክፍያዎች መሆን አለባቸው ፡፡

9. <u>የኢንተርኮኔክሽን መብቶች እና ግዴታዎች</u>

1) አንድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ጥቅም ላይ ያዋለው ደጋፊ ቴክኖሎጂ ከግምት ውስጥ ሳይገባ ከሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎቶች የመጠየቅ መብት እና ሲጠየቅ ስለኢንተርኮኔክሽን የመደራደር እና በቴክኒክ ደረጃ አዋጪ በሆኑ አካባቢዎች ኔትዎርኩን የማገኛኘት ግዴታ አለበት፡፡

2) አገናኝ ኦፕሬተሮች የእያንዳንዳቸውን የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ኔትወርክ ለማቀድ፣ ለመገንባት፣ ለመዘርጋት ወይም ለመጠበቅ አንዱ ከሌላው መረጃ የመጠየቅ እና የመቀበል መብት አላቸው፡፡

3) አገናኝ ኦፕሬተሮች በዚህ መመሪያ መሠረት የተቀበሉትን መረጃ ለተጠየቀበት ዓላማ ብቻ መጠቀም እና የመረጃውን ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ ተገቢውን ጥረቶች ማድረግ አለባቸው፡፡

## ክፍል አራት
## የኢንተርኮኔክሽን ሥነ ሥርዓቶች

10. <u>በቅን ልቦና የሚደረግ ድርድር</u>

1) የኢንተርኮኔክሽን ስምምነቶች ላይ የሚደረግ ድርድር በተሳታፊ ኦፕሬተሮች መካከል በቅን ልቦና መካሄድ አለበት፡፡ እንዲሁም አገናኝ ኦፕሬተሮች ከኢንተርኮኔክሽን ጋር የተያያዙ አለመግባባቶችን ለመፍታት ተገቢውን ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡

2) በቅን ልቦና የሚደረጉ ድርድሮች እያንዳንዱ ተደራዳሪ ወገን የሚከተሉትን ማድረግ እንደሌለበት ያመለክታሉ፤

   (ሀ) ሌላኛውን ወገን ሆን ብሎ ማሳሳት፤

   (ለ) ሌላውን ተዋዋይ በኃይል ወይም በመጫን ስምምነት ላይ እንዲደርስ ማስገደድ፤ እና ፣

   (ሐ) ሆን ብሎ ድርድርን ማደናቀፍ፤

3) በቅን ልቦና የመደራደር መርሆዎችን መጣስ የሚከተሉትን ያካትታል፤

   (ሀ) ለሌላው ኦፕሬተር አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች ሁሉ በወቅቱ አለመስጠትን፤

   (ለ) ጫና የሚያሳድሩ ወይም ያለአግባብ የተለጠጡ ወይም ገደብ የሚጥሉ ሚስጥርን ያለመግለጽ ስምምነቶች እንዲፈረሙ ማስገደድን፤

   (ሐ) ለወደፊት ማሻሻያዎችን ለማድረግ የሚፈቅድ ድንጋጌ በስምምነት ውስጥ እንዳይካተት መቃወምን፤

   (መ) በስምምነቱ ውስጥ የተካተቱትን ድንጋጌዎችና ሁኔታዎች ከጉዳዩ ጋር የማይዛመዱ ጉዳዮችን እልባት ከመስጠት ጋር ለማያያዝ መሞከርን፤

   (ሠ) ገዥ ውሳኔዎችን ለመፈጸም ሥልጣን ያለውን ሰው ለመሰየም በተደጋጋሚ ፈቃደኛ አለመሆንን ጨምሮ እና በዚህም ሳይወሰን ድርድርን የማዘግየት ድርጊቶችን መፈጸምን፤ እና

(ረ) ባለሥልጣኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚወስናቸውን ሌሎች ጉዳዮችን፤

11. <u>የኢንተርኮኔክሽን ጥያቄ</u>

1) አንድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ለሌላ ኦፕሬተር የኢንተርኮኔክሽን ጥያቄ ሲያቀርብ ጥያቄውን እንደሚከተለው ማቅረብ ይኖርበታል፤

(ሀ) ለተጠያቂው ኦፕሬተር በጽሑፍ ማቅረብ ፣

(ለ) የኢንተርኮኔክሽን ቅጽ፣ ድርድሩን ለመጀመር የታሰበበትን ቀን፣ ኢንተርኮኔክሽኑ የሚፈለግበትን ቀን፣ እንዲሁም የሚያስፈልገውን የኢንተርኮኔክሽን አቅም ግምትን ጨምሮ በእነዚህም ሳይወሰን በቂ መረጃዎችን ማቅረብ፤ እና

(ሐ) ለባለሥልጣኑ ጥያቄውን በአምስት (5) የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ማሳወቅ፡፡

2) ተጠያቂው ኦፕሬተር የኢንተርኮኔክሽን ጥያቄን በተቀበለ በአሥራ አምስት (15) የሥራ ቀናት ውስጥ የሚከተሉትን መፈጸም ከቻለ ለጠያቂው ኦፕሬተር በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል

(ሀ) ከኢንተርኮኔክሽን ጋር የተያያዙ ደርድሮችን በታቀደው ቀን መጀመር፤

(ለ) የተጠየቀውን የኢንተርኮኔክሽን ቅጽ ማቅረብ፤ እና

(ሐ) በጠያቂው ኦፕሬተር በቀረበው የጊዜ ገድብ ውስጥ ኢንተርኮኔክሽኑን ማከናወን፤

3) ተጠያቂው ኦፕሬተር የተጠየቀውን ኢንተርኮኔክሽን ለማቅረብ የሚችል መሆኑን ለጠያቂው ኦፕሬተር ከገለጸ የኢንተርኮኔክሽኑን አቅርቦት መነሻ ሰነድ ኮፒን በመስጠት የኢንተርኮኔክሽኑ ጥያቄ በቀረበ በአስራ አምስት (15) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ድርድርሩን መጀመር ይኖርበታል፡፡

4) ተጠያቂው ኦፕሬተር እና ጠያቂው ኦፕሬተር በቅን ልቦና መደራደርና ድርድሩን ለማጠናቀቅ የሚቻላቸውን ሁሉ ጥረት በማድረግ ድርድርሩ በተጀመረ ሠላሳ (30) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ወይም ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በተስማሙበት ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መፈራረም ይኖርባቸዋል፡፡

5) የኢንተርኮኔክሽን ጥያቄ ከቴክኒክ አንፃር አዋጪ ሆኖ ካልተገኘ ወይም በባለሥልጣኑ እንደተወሰነው ካልሆነ ውድቅ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም ተጠያቂው ኦፕሬተር የምክንያቱን አሳማኝነት የኢንተርኮኔክሽን ጥያቄን በተቀበለ ከአሥራ አምስት (15) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በጽሑፍ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

6) ተጠያቂው ኦፕሬተር የኢንተርኮኔክሽኑን ጥያቄ ውድቅ የተደረገበትን ኮፒ ወይም ቅጂ ውድቅ የተደረገበት ውሳኔ ለጠያቂው ኦፕሬተር በደረሰው ሰባት (7) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በባለሥልጣኑ ፋይል ውስጥ እንዲያያዝ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

7) በአዋጁ አንቀጽ 43(2) መሠረት ተጠያቂው ኦፕሬተር የኢንተርኮኔክሽኑን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው እንደሆነ ወይም ተዋዋይ ወገኖቹ ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉ ወይም ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ኢንተርኮኔክሽኑ ካልተጠናቀቀ ከተዋዋዮቹ ወገኖች አንዱ ለባለሥልጣኑ ይግባኝ ማቅረብ ወይም ባለሥልጣኑ በራሱ ተነሳሽነት ጣልቃ በመግባት በአዋጁ ከአንቀጽ 35 እስከ አንቀጽ 38 ወይም ባለሥልጣኑ አለመግባባትን ለመፍታት ባወጣው መመሪያ መሠረት አስገዳጅ ውሳኔ መስጠት ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት
## የኢንተርኮኔክሽን ስምምነቶች

12. <u>የኢንተርኮኔክሽን ስምምነቶች</u>

1) በኦፕሬተሮች መካከል የሚደረጉ ሁሉም የኢንተርኮኔክሽን ስምምነቶች በጽሑፍ ሆነው፤

(ሀ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 እና አንቀጽ 8 የተነገሩትን መርሆዎች የተከተሉ፣

(ለ) በሁለቱም የኢንተርኮኔክሽን ተዋዋይ ወገኖች ፈቃዶች የተመለከቱትን ድንጋጌዎችና ሁኔታዎችን የሚያከብሩ ፣

(ሐ) በኢንዱስትሪው በስፋት ተቀባይነት ያገኙ ወይም በባለሥልጣኑ የፀደቁ ደረጃዎችን የሚያሟሉ፤ እና

(መ) ከአዋጁ፣ ከዚህ መመሪያ እና በባለሥልጣኑ ከወጣ ተፈጻሚነት ካለው ማናቸውም መመሪያ ጋር የተጣጣሙ፤

መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

2) የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት ጠያቂው ኦፕሬተር በህግ መሠረት መፈጸም የሚችለውን የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅርቦት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚገድብ ወይም እንዳይፈጸም የሚያደርግ መሆን የለበትም፡፡

13. <u>የኢንተርኮኔክሽን ስምምነትን ፋይል ስለማድረግ</u>

1) የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት ከተፈረመ በኋላ ተጠያቂው ኦፕሬተር የስምምነቱን ኮፒ ስምምነቱ በተፈረመ ሰባት (7) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በባለሥልጣኑ ፋይል እንዲያያዝ ማድረግ አለበት፡፡

2) ባለሥልጣኑ የስምምነቱን የውል ቃሎች እና ሁኔታዎችን መገምገም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ከኢንተርኮኔክሽኑ አፕሬተሮች ተጨማሪ መረጃዎች መጠየቅ ይችላል፡፡

3) ባለሥልጣኑ የአገናኝ አፕሬተሮችን የንግድ መረጃዎችን ሚስጥራዊነትን ለመጠበቅ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ፋይል የተደረገውን የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት በድረ ገጹ ላይ ሊያወጣ ይችላል፡፡ እንዲሁም የመረጃዎቹን ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ ተገቢውን ጥረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

14. <u>የኢንተርኮኔክሽን ስምምነቶች ስለማሻሻል</u>

1) የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት ተዋዋይ የሆኑ ወገኖች በጋራ ስምምነት ስምምነቱን ማሻሻል ወይም ማስተካከል ይችላሉ፡፡ የተሻሻለው ወይም የተስተካከለው ስምምነት ማሻሻያው በተደረገ ሰባት (7) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከባለሥልጣኑ ፋይል ጋር መያያዝ አለበት፡፡

2) በአዋጁ አንቀጽ 43(2) መሠረት ባለሥልጣኑ በራሱ ተነሳሽነት ወይም በኢንተርኮኔክሽን ስምምነት ተዋዋይ ወገኖች በአንዱ የቀረበን ጥያቄ በመከተል የኢንተርኮኔክሽኑን ስምምነትን ማሻሻል የሚችለው ስምምነቱ ወይም ድንጋጌው፤

(ሀ) ከአዋጁ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን ሲሆን፤

(ለ) ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ሲሆን፤

(ሐ) በባለሥልጣኑ ከጸደቀና ተፈጻሚነት ካለው ማንኛውም መመሪያ ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን ሲሆን፤ ወይም

(መ) የሕዝብን ጥቅም የማያስጠብቅ ሲሆን፤

ነው።

3) ባለሥልጣኑ ጣልቃ ለመግባት ሲወስን በአዋጁ አንቀጽ 36 እና አንቀጽ 37 መሠረት እና ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱትን ሥነ ሥርዓቶች በመከተል አግባብነት ያለውን ማሻሻያ ግልጽ በሆነ መንገድ መወሰን አለበት፤

(ሀ) በሥራ ላይ ያለውን የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት ለማሻሻል የቁጥጥር ሂደቱ መጀመሩን በጉዳይ ያገባኛል ለሚሉ ወገኖች በሕዝብ ማስታወቂያ ያሳውቃል፤ ማስታወቂያውም የትኛው የስምምነቱ ድንጋጌ፤

(1) ከአዋጁ ድንጋጌ ጋር እንደሚቃረን፤

(2) ከዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች ጋር እንደሚቃረን፤

(3) በባለሥልጣኑ ካፀደቀውና ተፈጻሚነት ካለው ማንኛውም መመሪያ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጋር እንደሚቃረን፤ ወይም

(4) የሕዝብን ጥቅም እንደማያስጠብቅ፤

የሚያሳይ ግልጽ መግለጫ የያዘ መሆን ይኖርበታል።

(ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከቱት መግለጫዎች የታሰበውን ማሻሻያ እና ለማሻሻያው የተሰጠውን አሳማኝ ምክንያት ማካተት ይኖርባቸዋል።

(ሐ) ባለሥልጣኑ በጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች ለስምምነቱ በማሻሻያነት በቀረበው ሃሣብ ላይ ምላሽ ወይም አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ከሃያ አንድ (21) የሥራ ቀናት ያላነሰ ጊዜ መስጠት ይኖርበታል።

(መ) ባለሥልጣኑ በጉዳዩ ያገባኛል ከሚሉ ወገኖች አስተያየቶችን ከተቀበለ በኋላ ከሃያ አንድ (21) የሥራ ቀናት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ የተቀበላቸውን አስተያየቶች በተመለከተ፤

(1) ለእያንዳንዱ አስተያየት ምላሽ በመስጠት የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤ ወይም

(2) ለእያንዳንዱ አስተያየት ምላሽ ይሰጣል፤ አስፈላጊ ከሆነ በስምምነቱ ላይ የተጠቆሙ ለውጦችን ያደርጋል፤ የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች በመጀመሪያው ዙር በተቀመጠው ተመሳሳይ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንደገና አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ይፈቅዳል።

(ሠ) ባለሥልጣኑ የመጨረሻ ውሳኔውን ከመስጠቱ በፊት በራሱ ሥልጣን ከሁለት ለበለጡ ዙሮች በጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች ማሻሻያዎች ወይም አስተያየቶች እንዲያቀርቡ ሊፈቅድ ይችላል።

(ረ) በቁጥጥሩ ሂደት ባለሥልጣኑ በተቀበለው አስተያየት ላይ የሰጠውን ምላሽ እና የመጨረሻውን ውሳኔ በድረ ገጹ ማውጣት ይኖርበታል።

(ሰ) በቁጥጥሩ ሂደት በጉዳዩ ያገባኛል በሚሉ ወገኖች ለባለሥልጣኑ የተሰጡ መረጃዎች ሚስጥራዊነትን በተመለከተ ባለሥልጣኑ የመረጃዎቹን ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ ተገቢውን ጥረት ማድረግ አለበት።

4) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌዎች የባለሥልጣኑን የመቆጣጠር እና የመከታተል ሥልጣኑን ተግባራዊ እንዳያደርግ የሚያደናቅፍ መሆን የለበትም፡፡

## 15. የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት መቋረጥ

1) የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት የሚቋረጠው በስምምነቱ የተመለከቱትን የውል ቃሎች በጥብቅ በመከተል መሆን አለበት፡፡

2) የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት ተዋዋይ ወገን የሆነ ስምምነቱን ማቋረጥ ከፈለገ የውሉን ማቋረጫ ምክንያቶች በመጥቀስ ለሌላው ወገን ከስልሣ (60) የሥራ ቀናት ያላነሰ ጊዜ በመሥጠት በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ የተፈጸመ ጥስት ካለ ማስጠንቀቂያ የሚሰጠው ኦፐሬተር ለሌላው ወገን ጥሰቱን እንዲያስተካክል ከሠላሣ (30) የሥራ ቀናት ያላነሰ ጊዜ መስጠት ይኖርበታል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ማስጠንቀቂያ የደረሰው ወገን ጥሰቱን ካላስተካከለ ማስታወቂያ የሰጠው ወገን ስምምነቱን ለማቋረጥ ወይም በባለሥልጣኑ የክርክር መፍቻ መመሪያ መሠረት ባለሥልጣኑ ጣልቃ እንዲገባ መጠየቅ ይችላል፡፡

3) የኢንተርኮኔክሽኑ ስምምነት የተቋረጠበት ተዋዋይ ወገን በባለሥልጣኑ የክርክር መፍቻ መመሪያ መሠረት ባለሥጣኑ ጣልቃ እንዲገባ መጠየቅ ይችላል፡፡

4) የዚህ መመሪያ ድንጋጌ ቢኖርም፣ የኢንተርኮኔክሽኑን ስምምነት ያቋረጠ ተዋዋይ ወገን ስምምነቱ በተቋረጠ ሰባት (7) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ እና ስምምነቱን የማቋረጥ ማስታወቂያ ኮፒ ለባልሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

## 16. የኢንተርኮኔክሽን መነሻ ሰነድ

1) በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ገበያዎች ለኢንተርኮኔክሽን አገልግሎቶች ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳላቸው በባለሥልጣኑ የተወሰነላቸው የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተሮች በሙሉ የኢንተርኮኔክሽን መነሻ ሰነድ እንዲፀድቅ በባለሥልጣኑ ዘንድ ፋይል ማድረግ አለባቸው፡፡ የኢንተርኮኔክሽን መነሻ ሰነዱ በባለሥልጣኑ ትዕዛዝ ከተሰጠበት በኋላ አርባ አምስት (45) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ፋይል መደረግ አለበት፡፡

2) የኢንተርኮኔክሽን መነሻ ሰነድ በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 6 እስከ 8 የተደነገጉትን የኢንተርኮኔክሽን ስምነቶች አጠቃላይ መርሆዎችን እና የዚህን መመሪያዎች ድንጋጌዎችን መከተል እና የሰነዱ አካል ማድረግ አለበት፡፡

3) ባለሥልጣኑ የቀረበለትን የኢንተርኮኔክሽኑን መነሻ ሰነድ መገምገም እና ለህትመት ብቁ መሆን አለመሆኑን መወሰን ወይም በቀረበው ሰነድ የተካተቱትን ድንጋጌዎችና ኔታዎች በስልሣ (60) የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ ጣልቃ በመግባት ማሻሻል ይኖርበታል፡፡ ባለሥልጣኑ እንዲጸድቅ የቀረበውን ጥያቄ በስልሳ (60) የሥራ ቀናት ውስጥ ውድቅ ካላደረገው ወይም ጣልቃ በመግባት የኢንተርኮኔክሽን መነሻ ሰነዱን ካላሻሻለው የቀረበው ሰነድ እንደፀደቀ ይቆጠራል፡፡

4) በባለሥልጣኑ በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር፣ የጸደቀ የኢንተርኮኔክሽን መነሻ ሰነድ የተሻሻለ የኢንተርኮኔክሽን መነሻ ሰነድ እስከሚፀድቅ ድረስ ፀንቶ ይቆያል፡፡

5) የፀደቀ የኢንተርኮኔክሽን መነሻ ሰነድ የያዘ ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው ኦፐሬተር የተሻሻለ የኢንተርኮኔክሽን መነሻ ሰነድ እንዲፀድቅ በባለሥልጣኑ ዘንድ ፋይል ማድረግ አለበት፡፡

6) ባለሥልጣኑ የተሻሻለውን የኢንተርኮኔክሽን መነሻ ሰነድ በመገምገም ለህትመት እንዲበቃ የሚያፀድቀው መሆን አለመሆኑን በሠላሳ (30) የሥራ ቀናት ውስጥ መወሰን ይኖርበታል፡፡ ባለሥልጣኑ እንዲጸድቅ የቀረበውን ጥያቄ በሰላሣ (30) የሥራ ቀናት ውድቅ ካላደረገው ወይም ጣልቃ ገብቶ ሰነዱን ካላሻሻለው የተሻሻለው የኢንተርኮኔክሽን መነሻ ሰነድ እንደፀደቀ ይቆጠራል፡፡

7) ባለሥልጣኑ በእርሱ ዘንድ ፋይል የተደረገውን ወይም የፀደቀውን የኢንተርኮኔክሽን መነሻ ሰነድ ድንጋጌዎችና ሁኔታዎች፤

(ሀ) የኢንተርኮኔክሽን መነሻ ሰነድ ወይም የሰነዱ ማናቸውም ድንጋጌ ከአዋጁ፣ ከዚህ መመሪያ ወይም በባለሥልጣኑ ከፀደቀና ተፈጻሚነት ካለው ማናቸውም መመሪያ ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን ሆኖ ከተገኘ፤

(ለ) ባለሥልጣኑ ጣልቃ መግባቱ ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ፡፡

በራሱ ተነሳሽነት ወይም ከቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የቀረበን ጥያቄ መሠረት በማድረግ ጣልቃ በመግባት ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

8) ባለሥልጣኑ በእርሱ ዘንድ ፋይል የተደረገውን ወይም የፀደቀውን የኢንተርኮኔክሽን መነሻ ሰነድ ጣልቃ በመግባት ለማሻሻል ከወሰነ በአዋጁ አንቀጽ 36 እና አንቀጽ 37 መሠረት እና ከዚህ በታች የተመለከቱትን በመከተል ተገቢ የሆኑትን ማሻሻያዎች ግልጽ በሆነ አሠራር መወሰን አለበት፤

(ሀ) የኢንተርኮኔክሽን መነሻ ሰነዱን ለማሻሻል የቁጥጥር ሂደት መጀመሩን የሕዝብ ማስታወቂያ በማውጣት በጉዳዩ ያገባኛል ለሚሉ ወገኖች ያሳውቃል፡፡ ማስታወቂያውም የትኛው ድንጋጌ እንደሚሻሻልና ለምን እንደሚሻሻል የሚያሳይ ግልጽ የሆነ መግለጫ የያዘ ሆኖ ሰነዱ፤

(1) በአዋጁ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን መሆኑን፤

(2) ከዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን መሆኑን፤ ወይም

(3) በባለሥልጣኑ በፀደቀ ተፈጻሚነት ካለው ማንናውም መመሪያ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን መሆኑን፤

(4) የሕዝብን ጥቅም የማያስጠብቅ መሆኑን፤

ማሳየት ይኖርበታል፡፡

(ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8) የተመለከተው መግለጫ በማሻሻያነት የቀረበውን ሃሣብ እና የማሻሻያውን አሳማኝ ምክንያቶች ያካተተ መሆን አለበት፡፡

(ሐ) ባለሥልጣኑ በጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች በማሻሻያ ሃሣቡ ላይ ምላሽ እና አስተያየት እንዲሰጡ ከሃያ አንድ (21) የሥራ ቀናት ያላነሰ ጊዜ መስጠት ይኖርበታል፡፡

(መ) ባለሥልጣኑ በጉዳዩ ያገባኛል ከሚሉ ወገኖች አስተያየት ከተቀበለ በኋላ በተቀበለው አስተያየት ላይ ምላሹን ከሃያ አንድ (21) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ መስጠት ይኖርበታል፡፡ በምላሹም፤

(1) ለእያንዳንዱ አስተያየት ምላሽ በመስጠት የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤ ወይም

(2) ለእያንዳንዱ አስተያየት ምላሽ ይሰጣል፣ አስፈላጊ ከሆነ በቀረበው ሃሣብ ላይ ማሻሻያ በማድረግ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በጉዳዩ

ያገባኛል የሚሉ ወገኖች በመጀመሪያው ዙር በተቀመጠው ተመሳሳይ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንደገና አስተያየት እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡

(ሠ) ባለሥልጣኑ የመጨረሻ ውሳኔውን ከመስጠቱ በፊት በራሱ ሥልጣን ከሁለት ለበለጡ ዙሮች በጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች ማሻሻያዎች ወይም አስተያየቶች እንዲያቀርቡ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

(ረ) በቀጥጥሩ ሂደት ባለሥልጣኑ በተቀበለው አስተያየት ላይ የሰጠውን ምላሽ እና የመጨረሻውን ውሳኔ በድረ ገጹ ማውጣት ይኖርበታል፡፡

ሰ) በቁጥጥሩ ሂደት ወቅት በጉዳዩ ያገባኛል በሚሉ ወገኖች ለባለሥልጣኑ የተሰጡ መረጃዎች በሚስጥርነት መጠበቅ እስካለባቸው ድረስ ባለሥልጣኑ የመረጃዎቹን ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ ተገቢውን ጥረት ማድረግ አለበት፡፡

9) የኢንተርኮኔክሽን መነሻ ሰነድ የሚቀርበውን የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎቶች ዝርዝር ድንጋጌዎችና ሁኔታዎችን፣ የቴክኒክ ደረጃዎች እንዲሁም በኢንተርኮኔክሽን አገልግሎቶች አቅራቢ የሚተገበሩ የደህንነት ደረጃዎችን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

10) የኢንተርኮኔክሽን መነሻ ሰነድ የአገልግሎት ድንጋጌዎችና ሁኔታዎች እንዴት እንደሚሻሻሉ የሚገልጽ ድንጋጌዎችን ማካተት አለበት፡፡

11) የኢንተርኮኔክሽን መነሻ ሰነድ ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤

(ሀ) የስምምነት ማዕቀፍ ፤

(ለ) የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎቶች መግለጫ፤

(ሐ) ለቁሳዊ ኮሎኬሽን ዓላማ ሁሉም የኢንተርኮኔክሽን ቦታዎች እና የተደራሽነት ሁኔታዎች መግለጫ፤

(መ) ውጤታማ የሆነ ኢንተርኮኔክሽንን ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉ የቴክኒክ መስፈርቶች፤

(ሠ) ለኔትወርክ ግንኙነት የሚያገለግሉ የማሠራጫ ቴክኖሎጂዎች የቴክኒክ ዝርዝሮች፣ የቴክኒክ ደረጃዎች ወይም ቋሚ የአሠራር ደንቦች/ፕሮቶኮሎች/፤

(ረ) የመጀመሪያ ኢንተርኮኔክሽን አተገባበር ሥነ ሥርዓቶች እንዲሁም የአሠራር ሂደቶች፣ ተግባራዊ ሙከራዎች፤ ቀጣይነት ያለው የአገልግሎት አሰጣጥ፤ ዕቅድን፣ የኔትወርክ ትራፊክን እና የብልሽት አያያዝን እና የጥገና ሥርዐቶችን

(ሰ) የአንድ ጊዜ ክፍያዎችን፣ ተደጋጋሚ ክፍያዎችን፣ ክፍያዎችን፣ የክፍያ ሥርዐቶችን እና የውል ቃሎችን እና ሁኔታዎችን ጨምሮ ንግድ ነክ ጉዳዮች፤

(ሸ) የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎቶችን ማቅረቢያ የጊዜ ገደብን ፣ የአገልግሎት ጥራት መስፈርቶችን እና ግዴታን ባለማክበር የሚጣሉ መቀጮዎችን ያካተተ የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ ስምምነት፡፡

## ክፍል ስድስት
## የኢንተርኮኔክሽን ክፍያዎች

### 17. <u>የኢንተርኮኔክሽን ክፍያዎች</u>

1) ለኢንተርኮኔክሽን አገልግሎት የሚከፈል ክፍያ፤

(ሀ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 እስከ 8 በተመለከቱት መርሆዎች መሠረት፤

(ለ) ጠያቂው ኦፐሬተር ለተጠየቁት አገልግሎቶች የግድ አስፈላጊ ላልሆኑ የኔትወርክ ዘርፎች ወይም ዝግጅቶች ክፍያ እንዳይፈጽም እያንዳንዱን አገልግሎት በበቂ ሁኔታ ተነጣጥለው እንዲደራጁ የሚያደርግ፤ እና

(ሐ) በአዋጁ አንቀጽ 45 እና በባለሥልጣኑ በፀደቀው መመሪያ መሠረት ሕጋዊነት ያለው፤

መሆን ይኖርበታል፡፡

2) የኢንተርኮኔክሽን ክፍያዎች ተለይተው፤

(ሀ) ለቁሳዊ ኢንተርኮኔክሽን ማቋቋሚያ እና ማስፈጸሚያ ቋሚ የአንድ ጊዜ ክፍያዎች፤

(ለ) ጥቅም ላይ እየዋለ ላለ መሣሪያ፣ የኔትወርክ ክፍል ወይም መገልገያዎች በየጊዜው የሚከፈሉ ክፍያዎች፤

(ሐ) ለትራፊክ ማስተላለፊያ በአቅም ወይም በአጠቃቀም ላይ የተመሠረቱ ክፍያዎች፤ እና

(መ) ለተጨማሪ አገልግሎቶች የሚከፈሉ ተለዋዋጭ ክፍያዎች፤

ራሳቸውን ችለው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

3) ባለሥልጣኑ የኢንተርኮኔክሽን አገልገሎቶች አቅራቢ አገልግሎቶቹን በማቅረብ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው የወሰነ እንደሆነ ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው ኦፐሬተር የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎት ታሪፎቹ እንዲፀድቅለት ባለሥልጣኑ ዘንድ ፋይል ማድረግ አለበት ፡፡

4) በአዋጁ አንቀጽ 45 (4) መሠረት ባለሥልጣኑ ታሪፉን እስከሚያፀድቀው ድረስ ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው ኦፐሬተር ማናቸውንም ታሪፍ ከትግበራ እንዲያዘገይ መመሪያ ሊሰጥ ይችላል፡፡

5) ባለሥልጣኑ የኢንተርኮኔክሽን ታሪፎችን እንዲያጸድቅ የቀረበለትን ጥያቄ በተቀበለ በሰላሣ (30) የሥራ ቀናት ውስጥ ታሪፎቹን በማጽደቅ ወይም በአዋጁ አንቀጽ 46 መሠረት ታሪፎቹን ለመገምገም እና ሕጋዊነታቸውን ለማረጋገጥ የቁጥጥር ሂደት መጀመሩን በጽሑፍ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡

6) ባለሥልጣኑ የኢንተርኮኔክሽን ታሪፎቹ እንዲፀድቁ ለቀረበው ጥያቄ በሠላሳ (30) የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልሰጠ ታሪፎቹ እንደፀደቁ ይቆጠራሉ፡፡

7) ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 46 መሠረት የቁጥጥር ሂደቱን ለመጀመር ከወሰነ በአዋጁ አንቀጽ 36 እና አንቀጽ 37 መሠረት እና ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱትን ሥነ ሥርዐቶች በመከተል ውሳኔ ይሰጣል፤

(ሀ) መደበኛ የአሠራር ሂደትን በመከተል በአዋጁ አንቀጽ 45 መሠረት የኢንተርኮኔክሽን ታሪፎችን ለመገምገም እና ሕጋዊነታቸውን ለማረጋገጥ የቁጥጥር ሂደት መጀመሩን የሕዝብ ማስታወቂያ በማውጣት በጉዳዩ ያገባኛል ለሚሉ ወገኖች ያሳውቃል፡፡

(ለ) የሕዝብ ማስታወቂያውም የኢንተርኮኔክሽን ታሪፍ ግምገማን ባህርይን እና ሕጋዊ ነው በሚለው ደረጃ ታሪፎቹን ለመወሰን ባለሥልጣኑ የሚከተለውን አካሄድ ከሚያሳይ መግለጫ ወይም የመወያያ ወረቀት ጋር መቅረብ አለበት፤

(ሐ) ማስታወቂያው ፋይል የሚደረግበትን መስፈርቶች እና የህዝብ ውይይት የሚካሄድበትን ጊዜ የያያዘ ሆኖ በጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች አስተያየታቸውን ሊያቀርቡ የሚችሉበትን ጊዜ ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡

(መ) ባለሥልጣኑ በጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች በመወያያ ሰነዱ ላይ ምላሽና አስተያየት እንዲሰጡ ከሃያ አንድ (21) የሥራ ቀናት ያላነሰ ጊዜ መስጠት ይኖርበታል፡፡

(ሠ) ባለሥልጣኑ በጉዳዩ ያገባኛል ከሚሉ ወገኖች አስተያየቶች ከተቀበለ በኂላ ከሠላሳ (30) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፤

(1) ለእያንዳንዱ አስተያየት ምላሽ በመስጠት የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤

(2) ለእያንዳንዱ አስተያየት ምላሽ በመስጠት የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤ አስፈላጊ ከሆነ የተሻሻለ የመወያያ ሰነድ ያቀርባል፤ የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች አስተያየት እንዲሰጡ ከሃያ አንድ (21) የሥራ ቀናት ያላነሰ ጊዜ ይሰጣቸዋል፡፡

(ረ) ባለሥልጣኑ የመጨረሻ ውሳኔውን ከመስጠቱ በፊት በራሱ ሥልጣን ከሁለት ለበለጡ ዙሮች/ጊዜያቶች በጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች ማሻሻያዎች ወይም አስተያየቶች እንዲያቀርቡ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

8) የአንቀጽ 17 ከንዑስ አንቀፅ 1 እስከ 7 የተደነገጉት ቢኖሩም፣ ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 46፣ በዚህ መመሪያ ወይም በባለስልጣኑ በፀደቀ ማናቸውም መመሪያ መሠረት በራሱ ሥልጣን በማናቸውም ጊዜ ማናቸውንም የኢንተርኮኔክሽን ታሪፍ ለመገምገም እና ሕጋዊነቱን ለማረጋገጥ የቁጥጥር ሂደቱን ማከናወን ይችላል፡፡

9) በአዋጁ አንቀጽ 45 መሠረት ባለሥልጣኑ የታሪፎችን ሕጋዊነት ለማረጋገጥ እና የኢንተርኮኔክሽን ክፍያዎችን ለመወሰን ደረጃዎችንና ሥርዓቶችን የሚደነግጉ መመሪያዎችን ማውጣት ይችላል፡፡

## 18. የሂሳብ መዝገብ መለያየት

1) የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችን በችርቻሮ የሚሰጥ ከሆነ ፣ የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢው የአገልግሎቶቹ አካል የሆኑትን ወጪዎችና ገቢዎች ሁሉ ለመለየት የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎቶቹን በሕግ መሠረት ራሱን ችሎ እንደሚያከናውን ኩባንያ በተለዩ የሂሣብ መዝገቦች መያዝ ይኖርበታል፡፡

2) ባለሥልጣኑ የችርቻሮ አገልግሎቶች በሚሰጡ የኢንተርኮኔክሽሰን አቅራቢዎች የሂሳብ መዝገብ መለያየት እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን የሚደነግጉ መመሪያዎችን በራሱ ሥልጣን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል ሰባት
## የኢንተርኮኔክሽን የቴክኒክ ጉዳዮች

## 19. የኢንተርኮኔክሽን ቦታዎች

1) ጠያቂው ኦፕሬተር ተጠያቂው ኦፕሬተር የኢንተርኮኔክሽን ቦታዎችን ለማዘጋጀት የሚያስችሉ የሥርዓት ሁኔታዎች እና ሌሎች መስፈርቶችን ለመገምገም

እንዲያስችለው ኢንተርኮኔክት ለማድረግ ስለሚፈልገው ቦታ ወይም ቦታዎች የተሟላ ዝርዝር ለጠያቂው ኦፕሬተር ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

2) የኢንተርኮኔክሽን ቦታዎች የኢንተርኮኔክሽን ጥያቄዎችን ተከትሎ በተቻለ ፍጥነት መዘጋጀት አለባቸው፡፡

3) በባለስልጣኑ በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር አገናኝ ኦፕሬተሮች የራሳቸውን የኔትወርክ ትራፊክ ወደ ኢንተርኮኔክሽን ቦታ የማጓጓዣ ወጪን ጨምሮ ለግንባታ ወጭ እና የኔትወርክ ግንኙነትን ለመደገፍ ከተጓዳኝ መሣሪያዎች እና የማዞሪያ አቅም ጋር የራሳቸውን የኢንተርኮኔክሽን ቦታዎች የመጠገን ሃላፊነት አለባቸው፡፡

4) ጠያቂው ኦፕሬተር የኢንተርኮኔክሽን አገልገሎቶቹ ከተጠያቂው አገልግሎቶች እና ቅጥር ግቢዎች እንዲተሳሰሩለት ከጠየቀ የማስተሳሰሩ አገልግሎት የሚሰጥ ሆኖ፣ በባለሥልጣኑ በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር፣ የአገልግሎቱ ክፍያ በተዋዋይ ወገኖቹ በጋራ ስምምነት የሚወሰን ይሆናል፡፡

20. <u>የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ለኢንተርኮኔክሽን አገልግሎት</u>

1 በአዋጁ አንቀጽ 44(6) መሠረት የመሠረተ ልማት መጋራት በቋሚና በገባሪ መሠረተ ልማቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

2) የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አስፈላጊ በሆነው መጠን የኢንተርኮኔክሽን ስምምነቶች እና የኢንተርኮኔክሽን መነሻ ሰነድ የሚቀርበውን የኮሎኬሽንና የመሠረተ ልማት መጋራትን እና የአደረጃጀቱን ድንጋጌዎችና ሁኔታዎችን ዝርዝር ማካተት አለበት፡፡

3) የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት አገናኝ ኦፕሬተሮች ለአገልግሎቶች እና ለሥራ ቦታዎች ተደራሽ ለመሆን የሚከተሉትን ሥርዓት ማካተት አለበት፡፡ በተጨማሪምመሳሪያዎችን አዳብሎ ለማስቀመጥ የሚከተሉትን ሥርዓት የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ማካተት አለበት፡፡

4) የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎት ስምምነት አገልግሎቶቹ ስለሚገኙበት አካባቢ በቂ መረጃ እና ለመጋራት ያለውን አቅም እንዲሁም ቁልፍ ለሆነ መሠረተ ልማት ተደራሽነት የሚጠየቀውን የዋጋዎች ዝርዝር የሚያካትት መሆን አለበት፡፡

5) የኮሎኬሽን ድንጋጌዎች እና ሁኔታዎች እና የመሠረተ ልማት መጋራት አደረጃጀቶች በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 6 እስከ 8 እና በባለሥልጣኑ የጸደቀ ተፈጻሚነት ያለው መመሪያ የተደነገጉትን የግልጽነት፣ የአድልዎ አለማድረግ እና የክፍያ ሕጋዊነት መርሆዎችን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

6) በአዋጁ አንቀጽ 44 መሠረት የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎትን ለሕዝብ ለማቅረብ ዓላማ ባለሥልጣኑ አግባብ ባለው ገበያ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው በወሰነው በሌላ ኦፕሬተር ቅጥር ግቢ ውስጥ የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያ በኮሎኬሽን ለማስቀመጥ መጠየቅ ይችላል፡፡

(ሀ) ጥያቄውን የተቀበለው ኦፕሬተር ከቴክኒክ አንፃር ተገቢ እስከሆነ ድረስ ጥያቄውን ማስተናገድ እና የኮሎኬሽን ስፍራ ሕጋዊ ታሪፍን በቅን ልቦና መደራደር አለበት፡፡

(ለ) ተዋዋይ ወገኖቹ ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉ ባለሥልጣኑ በአዋጁ ከአንቀጽ 35 እስከ 38 ወይም በባለሥልጣኑ በፀደቀ ተፈጻሚነት ባለው መመሪያ መሠረት

በራሱ ተነሳሽነት ወይም በተሳታፊዎቹ ተዋዋይ ወገኖቹ በአንዱ ጥያቄ የኮሎኬሽኑን ድንጋጌዎችና ሁኔታዎችን ለመወሰን ጣልቃ ሊገባ ይችላል፡፡

7) በአዋጁ አንቀጽ 44 (7) መሠረት አግባብ ባለው ገበያ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው የተቆጠረ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ከሌላ ኦፕሬተር ምክንያታዊ ጥያቄ ከቀረበለት ገባሪ እና ቋሚ መሠረተ ልማትን ሁለቱንም ማጋራት ይገደዳል፡፡

(ሀ) ጥያቄውን የተቀበለው ኦፕሬተር ከተክኒክ አንፃር ተገቢ እስከሆነ ድረስ ጥያቄውን ማስተናገድ እና የኮሎኬሽን ስፍራ ሕጋዊ ታሪፍን በቅን ልቦና መደራደር አለበት፡፡

(ለ) ተዋዋይ ወገኖቹ ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉ ባለሥልጣኑ በአዋጁ ከአንቀጽ 35 እስከ 38 ወይም በባለሥልጣኑ በፀደቀ ተፈጻሚነት ባለው መመሪያ መሠረት በራሱ ተነሳሽነት ወይም በተሳታፊዎቹ ተዋዋይ ወገኖቹ በአንዱ ጥያቄ የኮሎኬሽኑን ድንጋጌዎችና ሁኔታዎችን ለመወሰን ጣልቃ ሊገባ ይችላል፡፡

8) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) እና (7) ድንጋጌዎች ቢኖሩም፣ የቴሌኮሙኒከሽን ኦፐሬተር የኮሎኬሽን እና የመሠረተ ልማት መጋራት ጥያቄ በባለሥልጣኑ አግባብ ባለው ገበያ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው ላልወሰነለት የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር እንዳያቀርብ የሚከለክለው ምንም ነገር አይኖርም፡፡ ጥያቄው በቀረበ ጊዜ ተዋዋይ ወገኖቹ በኮሎኬሽን እና በመሠረተ ልማት መጋራት የንግድ እና የቴክኒክ የውል ቃሎች ላይ መደራደር ይኖርባቸዋል፡፡

## 21. <u>የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎቶች ጥራት</u>

1) የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት መለስተኛ የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃዎችን የሚያካትት፣ ዓለም Xaቀፍ የኢንዱስትሪው ልምዶችን ያገናዘበ እና የአገልግሎት ደረጃዎችን ባለማሟላት ለሚፈጠር ችግር ተገቢ መፍሔዎችን የሚያስቀምጥ መሆን ይኖርበታል፡፡

2) የኢንተርኮኔክሽን ጥራት እና የአገልግሎት ደረጃ በተጠያቂው ኦፕሬተር የሚቀርብ የአገልግሎት ደረጃ ለራሱ ወይም ለሌላ ኦፕሬተር ከሚያቀርበው የጥራት እና የአገልግሎት ደረጃ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ለማረጋገጥ አድልዎ ካለማድረግ መርህ ጋር መጣጣም አለበት፡፡

3) የኢንተርኮኔክሽን አቅርቦት መነሻ ሰነድን ጨምሮ የኢንተርኮኔክሽን ስምምነቶች፤

(ሀ) የኢንተርኮኔክሽን ቦታዎች፣ የትራፊክ መስመሮች እና በኔትወርክ መሣሪዎች መካከል የሚደረግ የመረጃ ልውውጥ የመሳሰሉትን የአገልግሎት አቀራረብ እና የቴክኒክ ባህርያትን፤

(ለ) የአሠራርና የጥገና ሁኔታዎች እና ተዛማጅ የአፈጻጸም መለኪያዎችን፤

(ሐ) የአገልግሎት ጥራት አመላካቾች፤ እና

(መ) ክፍያዎች እና የአገልግሎት አስጣጥ ደረጃ ስምምነትን ባለማክበር የሚጣሉ መቀጮዎች፤

የሚገልጽ ወይም የሚደነግግ የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ ስምምነት ማካተት አለበት፡፡

## 22. <u>የኢንተርኮኔክሽን የቴክኒክ መስፈርቶች</u>

1) የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት ወይም የኢንተርኮኔክሽን አቅርቦት መነሻ ሰነድ ቢያንስ የሚከተሉትን ቴክኒካዊ መረጃዎች ማካተት አለበት፤

(ሀ) ቁሳዊ የኢንተርኮኔክሽን ዓይነት፤

(1) የቀረበውን ቁሳዊ የኢንተርኮኔክሽን ዓይነት ማለትም ኢንተርኮኔክሽን በተጠየቀው ኦፕሬተር ጣቢያ ወይም በጠየቀው ኦፕሬተር ጣቢያ ወይም በእያንዳንዱ ኦፕሬተር ጣቢያ መካከል፤

(2) ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች በኢንተርኮኔክሽን ቦታዎች ምርጫ ላይ ውጤታማ ምርጫ እንዲያደርጉ የሚያስችል ካርታን እና የኔትወርክ ንድፍን ጨምሮ ለኢንተርኮኔክሽን የቀረቡ የቦታዎች ዝርዝር፤

(3) ለእያንዳንዱ የኢንተርኮኔክሽን ቦታ አግባብነት ያላቸው የቴክኒክ መስፈርቶች እና ደረጃዎች በሙሉ፤

(4) ለኔትወርክ ዕቅድ አግባብነት ያላቸው የቴክኒክ መስፈርቶች እና ደረጃዎች በሙሉ፤

(5) በተጠያቂው ኦፕሬተር ኔትወርክ ውስጥ የኢንተርኮኔክሽን ቦታ ማቋቋም፣ ቦታ መቀየር ወይም ማንሳት ሥርዓቶች።

(ለ) የኢንተርኮኔክሽን ኔትወርክ ማዞሪያ

(1) ትራፊክን ለማገናኘት የሚያስፈልጉ የማዞሪያ አቅም መስፈርቶችን የማሟያ ደንቦች እና ሥርዓቶች፤

(2) የኢንተርኮኔክሽን ቦታዎች ማዞሪያ የሚከናወንበትን (ዓለም ዓቀፍ በር፣ የከተማ መገናኛ፣ የአገር ውስጥ ማዞሪያ ወዘተ.) ደረጃ መለየት ወይም አይፒ ኢንተርኮኔክሽንን በተመለከተ በየትኛው የትራንስፖርት ንብርብር ኢንተርኮኔክሽን እንደሚከናወን፤

(ሐ) ሊንክ እና ማስተላለፍ

የሁለቱን ኦፕሬተሮች ኔትወርኮችን የሚያገናኝ የኢንተርኮኔክሽን ሊንክ (ሀ) የትረፊክ መንገድን የመምረጥ አቅም(ለ) የማመላከቻው ስፋት፣ (ሐ) የማመላከቻው የተለያየ ባህርይ፤

(መ) ሲግናሊንግ

የሚገናኙ ኦፕሬተሮች በኢንዱስትሪው አጠቃላይ ተቀባይነት ካለው ዓለም ዓቀፍ ደረጃዎች ጋር በሚጣጣሙ የሲግናሊንግ ደረጃዎች ላይ መስማማት አለባቸው።

(ሠ) ኢንተርኦፐሬቢሊቲ

(1) የሚገናኙ ኦፕሬሮች ከአንዱ ጫፍ ወደ ሌላ ጫፍ የሚቀርቡት አገልግሎቶች የአስተማማኝነት ደረጃ የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፤

(2) የኔትወርክ አስተማማኝነትን እና የኢንተርኮኔክሽን ኢንተርኦፐሬቢሊቲ የሚከናወን ሥራን ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ የሚፈተሸበት ደንቦች እና ሥርዓቶች።

2) የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ በኢንተርኮኔክሽኑ አገልግሎቶች ላይ ሊደረጉ ስለታሰቡ ወይም ስለታቀዱ ማናቸውንም ለውጦች ለሚገናኘው ኦፕሬተር በቂ የሆነ የቅድሚያ

ማስጠንቀቂያ መስጠት እና በኢንተርኮኔክሽኑ አገልግሎት ላይ ጎጂ ውጤት የሚያስከትሉ ያልታሰቡ ለውጦችንም ለመቀነስ መጣር አለበት፡፡

23. <u>ስለቁጥር አሰጣጥ</u>

የሚገናኙ ኦፕሬተሮች አንዱ ለሌላኛው በየራሳቸው ኔትወርኮች ስላሉት ቁጥሮች መረጃ መሰጠት ይኖርባቸዋል፡፡

## ክፍል ስምንት
## ሕትመት

24. <u>በባለሥልጣኑ የሚታተም የኢንተርኮኔክሽን መረጃ</u>

1) ባለሥልጣኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ የኢንተርኮኔክሽን ስምምነቶችን እና የኢንተርኮኔክሽን አቅርቦት መነሻ ሰነድን ጨምሮ የተሟላ እና ወቅታዊ የሆኑ የኢንተርኮኔክሽን ጉዳዮችን የሚመለከቱ መረጃዎች ያሳትማል ወይም መታተማቸውን ያረጋግጣል፡፡

2) ባለሥልጣኑ የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ ለኢንተርኮኔክሽን አገልግሎት በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ አግባብ ባላቸው ገበያዎች ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው ከወሰነ የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢው የአገልግሎቶቹ ታሪፎች ባለሥልጣኑ ዘንድ ፋይል ማድረግ አለበት፡፡ ባሥልጣኑ መረጃዎቹን በራሱ ድረ ገጽ ሊያወጣው ይችላል፡፡

3) ሁሉም ኦፕሬተሮች ከባለሥልጣኑ ምክንያታዊ ጥያቄ ሲቀርብላቸው ኢንተርኮኔክሽንን የሚመለከቱ የተለዩ መረጃዎችን ሁሉ ለባለሥልጣኑ መስጠት አለባቸው፡፡ ባለሥልጣኑ የኢንተርኮኔክሽኑን ተዋዋይ ወገኖች የንግድ መረጃዎችን ሚስጥራዊነት መጠበቅን ትኩረት በመስጠት የመረጃዎቹን ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ ተገቢውን ጥረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ
## አለመግባባትን ስለመፍታት

25. <u>የኢንተርኮኔክሽን አለመግባባትን ስለመፍታት</u>

1) የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት ተዋዋይ ወገን የኢንተርኮኔክሽኑን ስምምነቱን ጥሷል ወይም የኢንተርኮኔክሽኑን ስምምነቱን አለአግባብ አቋርጧል ብሎ ካመነ ያለመግባባቱ ላይ ባለሥልጣኑ ጣልቃ እንዲገባ መጠየቅ ይችላል፡፡

2) ባለሥልጣኑ ጣልቃ እንዲገባ የቀረበውን የጽሁፍ ጥያቄ ተከትሎ ጥያቄውን በተቀበለ ሠላሳ (30) የሥራ ቀናት ውስጥ፤

(ሀ) ጣልቃ ለመግባት ወይም ላለመግባት ከመወሰኑ በፊት ከተዋዋይ ወገኖቹ ተጨማሪ መረጃዎችን የመጠየቅ፤

(ለ) ጣልቃ ላለመግባት ከወሰነ ላለመግባት የወሰነበትን ከእነ አሳማኝ ምክንያቱ በጽሑፍ የማስፈር፤ ወይም

(ሐ) በባለሥልጣኑ የክርክር መፍቻ መመሪያ በተደነገጉት ሥርዓቶች መሠረት ጣልቃ ለመግባት መወሰኑን፤

ለጠያቂው ወገን ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡

3) በክርክር መፍትሄ አሰጣጥ መመሪያ መሠረት በባለሥልጣኑ መካከል የኢንተርኮኔክሽን አለመግባባት በመፈታት ላይ እያለ በማንኛውም ሁኔታ ኢንተርኮኔክሽኑ አይቋረጥም ፡፡

## ክፍል አሥር
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

26. ማሻሻያ

ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በማናቸውም ጊዜ ከአዋጁ ድንጋጌዎች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ አባሪዎችን ጨምሮ ይህንን መመሪያ ማሻሻል ይችላል፡፡

27. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ ___ ቀን 2012 ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ _______ ቀን ________________

ኢንጂነር ባልቻ ሪባ
የኢትዮጵያ ኮሙኒከሽን ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር

## አባሪ ሀ
## የኔትወርክ ኢንተርኮኔክሽን አገልግሎት አይነቶች ማብራሪያ

የሚከተሉት የአገልግሎት ምድቦች የተለመዱ የኔትወርክ ኢንተርኮኔክሽን አይነቶችን ለማብራራት የቀረቡ ናቸው። ይህ ዝርዝር ተጓዳኝ አገልግሎቶችንም ሆነ በአጠቃላይ ኢንተርኮኔክሽንን ለማሳካት የሚያስፈልጉ የኮሎኬሽን አገልግሎቶችን አየካትትም።

1) **የመደበኛ ጥሪ ማገናኘት አገልግሎት ጅምላ ሽያጭ**: የመደበኛ ድምጽ አገልግሎት ለደንበኞቹ በሚያቀርብ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር (አገናኝ ኦፕሬተር) የሚሰጥ የጥሪ ማስተላለፍ አገልግሎትን ይመለከታል። አገልግሎቱ ለሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የሚሰጥ ሲሆን ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኝ ሌላ ኦፕሬተርንም ሊያካትት ይችላል። የአገናኝ ኦፕሬተር ኔትወርክ ከሌላ ኦፕሬተር ኔትወርክ የመጣውን ጥሪ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚመጡ ጥሪዎችን ጨምሮ በራሱ ኔትወርክ ላይ ጥሪዎችን በማስተላለፍ በተጠሪው ወገን ማለትም የአገናኝ ኔትወርክ ላይ ወደሚገኙ ደንበኞች ያገናኛል።

2) **የሞባይል ጥሪ ማገናኘት አገልግሎት ጅምላ ሽያጭ**: የሞባይል ድምጽ አገልግሎት ለደንበኞቹ በሚያቀርብ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር (አገናኝ ኦፕሬተር) የሚሰጥ የጥሪ ማስተላለፍ አገልግሎትን ይመለከታል። አገልግሎቱ ለሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የሚሰጥ ሲሆን ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኝ ሌላ ኦፕሬተርንም ሊያካትት ይችላል። የአገናኝ ኦፕሬተር ኔትወርክ ከሌላ ኦፕሬተር ኔትወርክ የመጣውን ጥሪ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚመጡ ጥሪዎችን ጨምሮ በራሱ ኔትወርክ ላይ ጥሪዎችን በማስተላለፍ በተጠሪው ወገን ማለትም የአገናኝ ኔትወርክ ላይ ወደሚገኙ ደንበኞች ያገናኛል።

3) **የአጭር መልዕክት አገልግሎት ማገናኘት አገልግሎት**: በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የሚሰጥ የመልዕክት አገልግሎት ነው። አገልግሎቱ ለሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የሚሰጥ ሲሆን ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኝ ሌላ ኦፕሬተርንም ሊያካትት ይችላል። የአገናኝ ኦፕሬተር ኔትወርክ ከሌላ ኦፕሬተር ኔትወርክ የመጣውን የአጭር መልዕክት አገልግሎት በራሱ ኔትወርክ ላይ የአጭር መልዕክት አገልግሎት በማስተላለፍ በተቀባዩ ወገን ማለትም የአገናኝ ኔትወርክ ላይ ወደሚገኙ ደንበኞች ያገናኛል።

4) **የመልቲሚዲያ መልዕክት አገልግሎት ማገናኘት አገልግሎት**: በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የሚሰጥ የመልዕክት አገልግሎት ነው። አገልግሎቱ ለሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የሚሰጥ ሲሆን ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኝ ሌላ ኦፕሬተርንም ሊያካትት ይችላል። የአገናኝ ኦፕሬተር ኔትወርክ ከሌላ ኦፕሬተር ኔትወርክ የመጣውን የመልቲሚዲያ መልዕክት አገልግሎት በራሱ ኔትወርክ ላይ የመልቲሚዲያ መልዕክት አገልግሎት በማስተላለፍ በተቀባዩ ወገን ማለትም የአገናኝ ኔትወርክ ላይ ወደሚገኙ ደንበኞች ያገናኛል።

5) **የትራንዚት ኢንተርኮኔክሽን ጅምላ ሽያጭ**: ጥሪው ከመጣበት አካባቢ ኔትወርክ በሌለው እና አገናኝ ኦፕሬተር ባልሆነ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የሚሰጥ የጥሪ ማስተላለፍ አገልግሎትን ያመለክታል። አገልግሎቱ ለሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ወይም ከኢትዮጵኣ ውጭ ለሚገኝ ሌላ ኦፕሬተር የሚሰጥ ነው።

6) **የመደበኛ ጥሪ ጅምላ ሽያጭ አቅርቦት አገልግሎት**: የመደበኛ ድምጽ አገልግሎት ለደንበኞቹ በሚያቀርብ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር (አቅራቢ ኦፕሬተር) የሚሰጥ የጥሪ ማስተላለፍ አገልግሎትን ይመለከታል። አቅራቢ ኦፕሬተር በራሱ ኔትወርክ ላይ ያለን ጥሪ ለትራንዚት ጅምላ ሽያጭ ወይም የጥሪ ማስተላለፍ ጅምላ ሽያጭ ወደ የኢንተርኮኔክሽን ቦታ ያስተላልፋል። የመደበኛ ጥሪ ጅምላ ሽያጭ አቅርቦት አገልግሎት አስተላላፊ የመምረጥ አገልግሎት አቅርቦትን ለማመቻቸት ያስችላል። ይህ አገልግሎት ከቴሌኮሙኒኬሽን

ኔትወርክ ጋር የተገናኙ ደንበኞች ለመደበኛ የድምጽ ጥሪ ሌላ አገልግሎት አቅራቢን መምረጥ የሚችሉበትን ዕድል ይሰጣል።

7) **የኢንተርኔት ትራንዚት አገልግሎት፡** የኢንተርኔት ትራንዚት አገልግሎት ወይም የአይፒ ትራንዚት አገልግሎት የጠያቂ ኦፕሬተር የኢንተርኔት ትራፊክ ከአለምአቀፍ የኢንተርኔት ትራፊክ ጋር መገናኘት እንዲችል በተጠያቂ ኦፕሬተር ለጠያቂ ኦፕሬተር የሚሰጥ አገልግሎትን ይመለከታል።

8) **በቀጥታ ዳታ የመለዋወጥ አገልግሎት፡** ሁለት የተለያዩ እራሳቸውን የቻሉ የቴሌኮሙኒኬሽኖች ኦፕሬተሮች በመካከላቸው ያለውን የዳታ ትራፊክ በቀጥታ የሚለዋወጡበት እና ከዓለም አቀፍ ኢንተርኔት ጋር የሚገናኙበት አገልግሎት ነው። በቀጥታ ዳታ የመለዋወጠ አገልግሎት ከክፍያ ነጻ ወይም በክፍያ ሊሆን ይችላል።